የልማት ጋዜጠኝነት ጊዜው ያልደረሰ ሀሳብ ፤ ወይስ የተሳካ ግብ ?

ዓለማየሁ ሞገስ *01-11-17*

(moges100@yahoo.com)

ምዕራባዊያን ባለፉት ሀምሳ አመታት የደሀ ሀገሮችን ችግር በመሰረታዊነት ለመፍታት በሚል በርካታ ያልተሳኩ ጥረቶች አካሂደዋል ፡፡ የድህነት መቀነሻ ስትራተጅዎችም ተነድፈው ተንቀሳቅሰዋል ፡፡ ምሁራንን በማስተባበርም አዳዲስ የልማት ንድፈ-ሀሳቦች አፍልቀዋል፡፡

የዕርዳታና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ዘርግተው የደሀ ሀገሮችን ኋላ ቀር ኢኮኖሚ እንዲያገግም ለማከም ሞክረዋል፡፡ አንዴ የችግሩ ምንጭ ለህዝቡ የስልጣን አለመጣጠን ሊሰመርበት ይገባል ሲሉ ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አይደለም፤ የደሀ ሀገሮች ሁነኛ ችግር ለህዝቡ የመረጃ ዕጥረት ነው ፤ ብለው መፍትሄ ያሉትን ሁሉ ሞክረዋል ፡፡ በአጠቃላይ ምዕራባዊያን የደሀ ሀገሮችን ችግር ለመፍታት ያላደረጉት ሙከራ የለም፡፡ አልተሳካላቸውም እንጅ፡፡

የአሁኖቹ ድንበር ተሻጋሪ ሚዲያዎችም ሆነ ዕርዳታ ለጋሽ ነን የሚሉ ኤጀንሲዎች በምዕራባዊያን ሀብታሞችና በሶስተኛው ዓለም ድሀ ሀገሮች መካከል የተፈጠረውን ክፍተት ለማጥበብ መፍትሄ ተብለው ከተቀየሱ ስትራተጅዎች ዋነኞቹ ናቸው ፡፡ ምዕራባዊ ድንበር ተሻጋሪ ሚድያዎችና አትራፊ ያልሆኑ የእርዳታ ኤጀንሲዎች ከ *1970* ዎቹ ጀምሮ በመደጋገፍ የደሀ ሀገሮች ችግር ፈች በመምሰል የንግድ ማስታወቂያና ገበያን በመጠቀም የገበያ አክራሪ ሀይሎችን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በመላው አለም ተቀባይነት እንዲቀዳጅ ከማድረግ ባለፈ ድህነትን በማቃለል የፈየዱት አንዳች ነገር እንደሌለ ታሪካቸውም ሆነ ተግባራቸው ይመሰክራል፡

ሁለቱ ሀይሎች በሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ዘንድ በማህበራዊ ግብይትና በማስታወቂያ ስራ ተነስተው የበለጸገውን አለም በተለይም የዋሽንግተን ስምምነት ማስፋትና ጥቅም በማስጠበቅ የነላ ሚና ሲጫወቱ መቆየታቸው ሌላው በመርዝ የተሸፈነ ተልዕኳቸው እንደሆነ በርካታ የምሁራን ሰነዶችን በዋቢነት ማቅረብ ይቻላል ፡፡

የምዕራባዊያን ሚድያዎችም ሆነ የረድኤት ኤጀንሲዎች በምዕራቡ ዓለምና በሶስተኛው አህጉር መካከል የተፈጠረውን የዕድገት ልዩነት ለማቀራረብ ሁነኛ መፍትሄ ያሉት የመረጃ አቅርቦትና ረድኤት ድርጅቶች የሚያቀርቡት የአቅም ግንባታ ድጋፍን ነበር ፡፡

ነገር ግን የሊበራል ሚዲያውም ሆነ ግብረሰናይ ድርጅቶች በመተባበር ባለፉት ሃምሳ ዓመታት የሶስተኛውን ዓለም ህዝብና መንግስት በዕርዳታ ስም እጅ በመጠምዘዝ የሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስከብር ፖሊሲ እንዲያራምዱ ከማሰገደድ ያለፈ የፈየዱት ነገር አልነበረም፡፡

ለዋቢነት ለረጅም ጊዜ ለቢቢሲ የምስራቅ አፍሪካ ዘጋቢ የነበረውን ግራሀም ሀንኩክ መጥቀሱ ሃሳቤን ያጎላዋል ብየ አምናለሁ፡፡ ግራሃም ሀንኮክ "የድህነት ከበርቴዎች" ወይም */Lords of the poverty/* በሚል ምጻት አዘል ርዕስ ባሳተመው መጻሀፉ ምዕራባዊያን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በአፍሪካ ፤ በላቲን አሜሪካም ሆነ በተቀሩት ደሀ የሩቅ ምስራቅ ሀገሮች ላይ ጥቅማቸውንና የፖለቲካ ኢኮኖሚ የበላይነታቸውን ለማስጠበቅና ማስቀጠል የቻሉት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስርዓትን በመንተራስ ነው ይላል፡፡

የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዙን ተግባር የእርዳታ ኢንደስትሪው ብቻውን እንዳልተወጣው ገራሀም ሀንኮክ ሳይደብቅ በግልጽ የጋዜጠኝነት ባህሪይው ያብራራል፡፡ ለምዕራባዊያን አከራሪ የገበያ ስርዓት በመላው አለም እንደልቡ እንዲጋልብ ዋነኛ መሳሪያው ድንበር ተሻጋሪ ሚዲያው መሆኑንም ሀንኮክ ያብራራል፡፡ የየሀገሬው ምሁራን */ national elits/* ለሊብራል ሚዲያውና ለረድኤት ድርጅቶች አጋፋሪ ከመሆን ያለፈ ሀገራቸውን ከድህነትና ኋላ-ቀርነት ለመታደግ አንዳችም ያበረከቱት አስተዋጽኦ አለመኖሩን በማስረገጥ፡፡

ከግራሀም ሀንኩክም ሆነ ሌሎች በርካታ ንድፈ-ሀሳባዊና ተግባራዊ ሰነዶች መረዳት የሚቻለው ፤ሂውማን ራይትስ ዎች፤ ሲ ፒ ጀ እንዲሁም ሊበራል ሚድያው በተለይ ቢቢሲ ፤ ሲ ኤን ኤን እና አልጀዚራ በሊበራል ገበያ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ማጧጧፍ እንጅ የድሀ ሀገር ማህበራዊ እና መረጃ ዕጥረት ችግር ፈችነት ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው አይፈቅድም፡፡

ምዕራባዊያን ግብረ ሰናይ ኤጀንሲዎችና ድንበር ዘለል ሚዲያዎች ከቅኝ ግዛት በኋላ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች በራሳቸው ጥረት የሚያደረጉትን መፍጨርጨር፤ የድህነት ቅነሳና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ከማገዝ ይልቅ በራስ ጥረት ከድህነት የመውጣት ሙከራን ለማምከን አፈር ሲበትኑበት ማየት የተለመደ አሰራራቸው ሆኖ ቆይቷል ፡፡

ይህ የሚዲያውም ሆነ የረድኤት ኤጀንሲዎች ደባ የኋላ ኋላ፤ በአንድ በኩል ደሀ ሀገሮች ከድህነት ለመውጣት በራሳቸው ጥረት የጀመሩትን የመልማትና መልካም አስተዳደር የማስፈን ጥረት ከማንም እጅ ሳይጠብቁ ራሳቸው ማከናወን እንደሚገባቸው ስንቅ ሲሆናቸው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሊበራል ሚዲያውም ሆነ ረጅ ተብዩ ድርጅቶች የገበያ አከራሪነትን

አይዲዮሎጅ ማስፋፋት እንጅ ለደሀ ሀገሮች የመረጃ ዕጥረትን ለማዳረስና የተራራቀውን የሀብት ልዩነት ለማቀራረብ ታሳቢ የማድረግ ግብም ዓላማም የሌላቸው መሆኑ ግልጽ እየሆነ ወጣ፡፡

ሊበራል ሚዲያው እነሱ "ጨለማው ዓለም" ብለው የሚጠሩት /አሁን የብርሀን ጭላንጭል ብቻ ሳይሆን የዓለምን የኢኮኖሚ አብላጫ ምህዳር ለመውሰድ እየተደረደረ ያለው/ ለድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎቻቸው ከጥሬ ዕቃና ጉልበት አቅራቢነት ያለፈ ሚና እንዳይጫወት ሌት ከቀን ሲሚደክም ይታያል፡፡

የገበያ አክራሪ ሚዲያው ሆነ የግብረ ሰናይ ኤጀንሲዎችን ያለፈውን የሃምሳ አመት የመረጃ አቅርቦትም ሆነ የዕርዳታና ብድር ታሪክ እንተወውና በቅርቡ ሀገራችን ስር ነቀል ማህበረ ኢኮኖሚ ለውጥ ያመጣሉ ብላ በጀመረቻቸው ሜጋ ፕሮጀክቶች ላይ ያሳዩትን አቋም ማንሳቱ ብቻ ተግባራቸው ባፈጠጠ ብልጠት ላይ የተንጠለጠለ መሆኑን ያሳያል፡፡

አጠቃላይ ማህበራዊ ይዞታችንን ስር-ነቀል በሆነ መንገድ የሚቀይሩ የሀይል ማመንጫዎች፤ ሰፋፊ እርሻዎች እና የድህነት መቀነሻ ሜጋ ፕሮጀክቶች በሚከናወኑበት ወቅት እነዚሁ የመረጃ አውታሮችና የዕርዳት ኤጀንሲዎች አንዱ አንባቢ ሌላው ተርጓሚ በመሆን ራሳቸውን ለግምት በሚዳርግ መንገድ ፕሮጀክቶችን የሚያብጠለጥል አጀንዳ ሲያራግቡ አስተውለናል፡፡

"በተበጣጠስ አነስተኛ አርሶ አደር ማሳ ልማት አይመጣም" ፤ ብሎ ሲያውጅ የነበረ ሀይል በሰፋፊ የእርሻ ማሳዎች ባለሀብቱ ሲሰማራ ደግሞ "የመሬት ወረራ በኢትዮጲያ " ብሎ አለማቀፍ ዜና ሽፋን ያደርጋል ፡፡

ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለጎረቤቶቻችንና ለአካባቢው ሀገሮች የኢኮኖሚ መነቃቃትና ዕድገት እንዲሁም ለሰላምና ትብብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ የታመነበትን የሃይል ማመንጫና ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ስንጀምር አንዴ ከቤተ -አምልኮ ጋር ሌላ ጊዜ ከአካባቢው ነዋሪዎች መፈናቀል ጋር እያላተሙ ዕርባና የለሽ አጀንዳቸውን ታዝበን አልፈናል፡፡ ለዚያውም የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ ዓይነት ግብረ-ሰናይ ኤጀንሲው ምስክር ሚዲያው (ቢቢሲ) አራጋቢ ሆነዋል ፡፡

ምዕራባዊያን ሚዲያዎችና ረድኤት ድርጅቶች በሀብታሙና ድሀው ክፍለ ዓለም የተፈጠረውን መራራቅ ለማቀረቀረብ ድሀ ሀገሮችን በማገዝ ከሆነ ለምን ኢትዮጲያ የጀመረቻቸውን የድህነት መቀነሻ ፕሮጀክቶች ከማብጠልጠል ይልቅ በዕድገታችን ላይ ሊያበረክት የሚገባውን ከፍተኛ ድርሻ አጉልተው ሽፋን አልሰጡም ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው ብየ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱ ግን ግልጽ ነበር ፤እነዚ ሚዲያዎች /news room/ በደሀ አገሮች ዘንድ የእርስ በርስ ግጭትና ረሀብ ዜና ሽፋን እንጅ፤ ስኬታማ ልማትና መልካም አስተዳደር ሽፋን ለመስጠት ተፈጥሯቸው ሊፈቅድላቸው አይችልም፡፡

ከተከበረው የሰው ልጅ ይልቅ ውሻ ሻወር ወስዶ ባለቤቱን ቀድሞ አልጋ ላይ በሚገኝበት ሀገር የሚሰራ ዓለማቀፍ ሚዲያ ለዘመናት የምግብ ዋስትናቸውን ሳያረጋግጡ አዲሱን ሚሊንየም የተቀላቀሉ አርብቶ አደሮችን ህይወት በመሰረታዊነት ከድህነት የሚያላቅቅ የሰፋፊ እርሻ እና የሀይል ማመንጫ ስራ ሲጀመር ነባሩ ባህላቸው ይዛነፋል ፤ ከቀያቸው ይፈናቀላሉ ወዘተ.. በመሳሰሉ ዕርባና- ቢስ ወሬዎችን በማሰራጨት ይጠመዳል፡፡

በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገሮች ኢትዮጲያን ጨምሮ ለችግራችን መፍትሄው የመረጃ ዕጥረትና የየፋይናንስ አቅም ውስንነት ነው፤ ለዚህም ከጎናችሁ እንቆማለን ካሉ በኋላ የሚነግሩን በሽታና የማታ ማታም ለፈውሱ የሚሰጡት ክትባት እጅግ የተለያየ መሆኑን በዓይናችን ታዝበናል፡፡

ሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ከተጨባጭ ማህበራዊ ይዞታቸው፤ ህብረተሰቡ በተጨባጭ ከሚከተለው የኢኮኖር ዘይቤ የተነጠለ

የፖለቲካ ኢኮኖሚ ዘይቤ እንዲከተልና ልቅ የገበያ መርህ እንዲያመልክ ለምን ይሰብካሉ ?

ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ወዲህ የግሎባላይዜሽንና ነጻ ገበያ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ በብቸኝነትም ባይሆን ስር መስደዱ የታሪክ አጋጣሚ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የምዕራባዊያን ስልጣኔ የሶስተኛው ዓለም ሀገሮችን ትኩረት እየሳበ መምጣቱ የሚካድ አይደለም ፤ ብቸኛና አማራጭ የሌለው ነበር ማለት ባይሆንም ፡፡

የነጻ-ገበያ ስርዓት በማን አለብኝነት ስር መስደድ ድሆች እጅግ እየደኸዩ፤ የበለጸጉት ደግሞ እጅግ እየበለጸጉና እየደለቡ

እንዲሄዱ እድል ሰጥቷል ፡፡ ሁሉም ነገር ለገበያው በተጣለበት ሁኔታ ብልጦች ብቻ የሚበለጽጉበትና እንዳሻቸው

የሚጋልቡት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ይሆናል ፡፡ ነጻ ገበያ ኢኮኖሚ በተግባር እንደሚታየው ጥቂት ስግብግቦች የሚገነቡት ካፒታል እንጅ መላ ህዝቡን ያሳተፈና በየደረጃው የልማቱ ተቋዳሽ የሚያደርግ ልማት አያስመዘግብም፡፡

የደሀ ሀገሮች ፖለቲካና ማህበራዊ መዋቅር ለገበያ አክራሪዎች የገበያ ስምሪት በሚመች መንገድ ካልተዋቀረ ጥቂት ብልጦች የሚያሸከረክሩትን የሊብራል ፖለቲካል- ኢኮኖሚያዊ ግስጋሴ መስናክል ይሆንብናል ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡

በኢኮኖሚ የበላይነታቸውን የሚፈታተን መዋቅራዊ ለውጥ የሚያስከትል ስርዓትም ሆነ አስተሳሰብ እንዳይመጣ ሊበራል ሚዲያውም ሆነ ሲቪክ ማህበራቶቻቸው አበክረው ይሰራሉ፡፡ ከገበያ አክራሪነት ወጣ ያለ አስተሳሰብና ተግባራዊ እንቅስቃሴ

ካዩ በአማኞቹ ዘንድ እምነት እንደታጣበት ጣዖት ሚዲያውና ግብረ-አበሮቹ ተባብረው በጋራ ቀጥቅጠው ያጠፉታል፡፡ ይህ አነዱ የዘላቂ ጥቅማቸው ማረጋገጫና የተለመደ መንገድ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት ደሀ ሀገሮች ከምዕራባዊያን የተለየ አይዲዮሎጅ እንዳያራምዱ ለምሳሌ እነደ ሀገራችን መንግስት በኢኮኖሚው የገላጋይነት / *enterventionist* / ሚና እንዳይጫወት የሞት-ሽረት ትግል ያካሂዳሉ ፡፡ የመንግስት ጣልቃ ገብነት የሚል ታርጋም ይለጥፉሉ፤ ነጻ-ገበያም እንደሌለ አድርግው በማወጅ ኢንቨስትመንትን ለማዳከም ይጥራሉ፡፡ ዕርዳታ ፤ብድር ፤የመረጃ እጥረት ወዘተ…የውሸት ጋጋታ ነው ፡፡

እንዲያውም እነዚህ የእርዳታ ኤጀንሲዎችም ሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ሚዲያ የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ከድህነት አዙሪት ውስጥ እንዳይወጡ ግፋ ቢል ከርካሽ ጉልበትና ጥሬ ዕቃ አቅራቢነት ያለፈ ሚና እንዳይኖራቸው አበክረው የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከሀገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ቀይሰው እንዲንቀሳቀሱ ከማገዝ ይልቅ የድህነታቸው ዘበኛ መንግስት መስርተው የነሱን ምጽዋዕት ጠባቂ እንዲሆኑ ይጥራሉ፡፡

የገበያ አክራሪ መርህን ተከትለው የተፈጠሩት የምዕራባዊያን ብዙሀን መገናኛ አውታሮች መላው ዓለም ተመሳሳይ የሚድያ መመዘኛ መስፍርት መጠቀም ይገባዋል የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡ደሀ ሀገሮችም ቢሆን ልማትና መልካም አስተዳደር ማስመዝገብ የሚችሉት ሊበራል ሚዲያ ዘውግ በመከተል ብቻ ነው፤ የሚሉት አነዚሁ ወገኖች የእነሱን ዱካ አለመከተል ነጻ አስተሳሰብን ማፈን ነው እስከሚል ጽንፍ ይደርሳሉ ፡፡

ሊበራል ሚዲያው በደሀና ሀብታም ሀገሮች መካከል የተፈጠረውን ክፍተት ከማጥበብ ይልቅ በተቃራኒው በመጓዝ ችግሩን ከመረጃና ከሀብት መራራቅ ባለፈ የአይዲዮሎጅ ችግር አድርጎታል የሚሉ ምሁራን ቁጥራቸው ብዙ ነው፡፡ እነዚህ ምሁራን የምዕራባዊያን ልቅ የሚድያ ፍልስፍና / *liberal media philosophy* / የፖለቲካ-ኢኮኖሚያቸው የካርቦን ቅጅ ወይም ነጻብራቅ የመሆኑን ያህል በታሪክ አጋጣሚ በዳበረ አሰራር የተካነና የልማት ጋዜጠኝነት / *development journalism* / የሚተገበርበትን ሶሰተኛው ዓለም አፈር ላይ ቀድሞ የመዘራት እድል አግኝቷል ፡፡

ለዚህ አንደኛው ምክንያት ሶሰተኛው ዓለም ሀገሮች በምዕራባዊያን ቅኝ መገዛታቸው እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ ፡፡ የሊበራል ሚዲያ መመዘኛ መስፍርቶች የልማት ጋዜጠኝነት ቀድሞ እየተተገበረ በሚገኝባት በሩቅ ምስራቋ አገር ፊሊፒንስ ምን ያህል ተጽዕኖ እየፈጠረ ስለመሆኑ በዘርፉ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራንን አስተያየት እያነሳን በጥቂቱ ለማየት እንሞክር ፡፡

ዶ/ር ክሪስቲ ማስሎግ ፊሊፒንስ በሚገኘው ሎሰ ባኖስ ዩኒቨርሲቲ የልማት ኮሚኒኬሽን አኒስቲትዩት ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ልማትና መልካም አስተዳደር ከሀገሬው ህዝብና ዕውቀት መቀዳት አለበት እንጅ እንደ ሸቀጥ ከውጭ የምናስገባው አይደለም የሚል ጠንካራ አቋም የሚያራምዱት ፕሮፌሰር ማስሎግ የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ አድቮኬተር ናቸው፡፡

የቀድሞው የልማት ጋዜጠኛ ፕሮፌሰር ክሪስቲ ማስሎግ የምዕራባዊያን ጋዜጠኝነት ዘውግ ቀድማ የልማት ጋዜጠኝነትን ተግባራዊ ማድረግ በጀመረችው ፊሊፒንስና በኤሽያ ምድር በኋላም በሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ላይ ያደረሰውን ብርቱ ተጽዕኖ ከራሱ ተሞክሮ ጭምር በርካታ ጥናታዊ ወረቀቶችን አቅርቧል፡፡

ማስሎግ በልማታዊ ሀገሮች ለሚተገበረው የልማት ጋዜጠኝነት የዘርፉ መመዘኛዎች ከሊበራል የሚዲያ አሰራር በተለየ መንገድ መታየት እንዳለባቸው ከሚተነትንባቸው ጥናቶቹ አንዱ ፡ "*Asian Value In Journalism: Idle Consept or realistic goal?*" የሚለው ጥናቱ ይገኝበታል፡፡

ዶ/ር ማስሎግ በዚህ ጥናታዊ ዳሰሳው በርካታ የሩቅ ምስራቅ ሀገሮች ትውልድ ሀገሩን ፊሊፒንስን ጨምሮ ማሌዝያ ፤ሲንጋፖር ሆንግ ኮንግ ፤ኢንድያ ፤ ቬትናምና ኢንዶኔሽ በምዕራባዊያን ቅኝ -ግዛት ስር አንደነበሩ ያስረዳል ፡፡ እነኚሁ ሀገሮች በቅኝ ገዥዎቻቸው ከደረሰባቸው ግፍ አንዱ የልማት ጋዜጠኞቻቸው የሊበራል ሚዲይ ዘውግን በቀኝ ገዥዎች ቅኝትና አመለካከት ሳያላምጡ እንዳለ መዋጣቸው ነው ይላል፡፡

ማስሎግ ከቅኝ ግዛት በኋላ ፊሊፒንስ ለዘረጋችው የድህነት ማቃለያ መርሀ-ግብር ሊሰራ የሚችለው የልማት ጋዜጠኝነት ዘውግ ሆኖ እያለ ፤ነገር ግን ሊበራል ወይም በእሱ አገላለጽ ከባዕድ ሀገር የተሸመተ ጋዜጠኝነት */ imported journalism/* እሴቶች በጋዜጠኞቻቸው እዕምሮ ቀድሞ ቦታ በመያዝ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞት እንደነበር ያብራራል፡፡

ዶ/ር ማስሎግ የሊበራል ሚዲያ እሴቶች የሚባሉት */accuracy, conflict, timeliness, prominence, sex nd oddity /*ትክክለኛነት ፤ ግጭት ፤ ወቅታዊነት ፤ የታላላቅ ሰዎች ውሎ ፤ የወሲብ ቅሌትና ወዘተ … በመሳሰሉ ልቅምቃሚ ቃላቶች የታጀበ ነው ይላል ፡፡

እንዲያውም ይላል ፤ክሪስቲ ማስሎግ ፤ እነዚህ የሊበራል ሚዲያና ኮሙኒኬሽን መመዘኛዎች የኤሽያን ነባረዊና ሁለንተናዊ ገጽታ በትክክል የማይገልጹ ይልቁንም የምዕራባዊያን የረጅም ጊዜ ሰፊ ቂም-በቀል */ broad vengeance/* መውጫ የማራመድ ተልዕኮ ያላቸው የቅኝ ግዛት ውርሶች */ colonial legacy /* መስፍርቶች ናቸው የሚል አቋም አስከማራመድ ይደርሳል ፡፡

የኤሽያ ጋዜጠኞች ስነ-ልቦና በሊበራል ጋዜጠኝነት ዘውግ መለከፍና ከቀኝ ግዛት በኋላ የኤሽያ ሀገሮች የሚከተሉትን ልማታዊ መንግስት / *Developmental state* / ፖለቲካል-ኢኮኖሚ በትክክል መግለጽ አለመቻል የዘርፉ ፈታኝ ሁኔታ ነበር፡፡

በምዕራባዊንና በሶስተኛው ዓለም ሀገሮች መካከል የተፈጠረውን የማህበረ ኢኮኖሚ መራራቅ በማጥበብ የራሱን ሚና ይጫወታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የልማት ጋዜጠኝነት " መልካም ዜና ሁሉ ዜና ዓይደለም፡፡" በሚለው የምዕራባዊያን ሊበራል ሚድያ ፍልስፍና መስፍርት ተቀስፎ ኤሽያዊያን የጀመሩትን ዘላቂ ልማትና ሰላም ሊያስተናግድ እንዳልቻለም ማስሎግ ያብራራል፡፡

አንደ ዶ/ር ማስሎግ ጥናት የኤሽያ ጋዜጠኞች ከነጻነት በኋላ በምዕራባዊያን የዜናና መጣጥፍ መስፍርቶች / ወንጀል፤ ግጭት፤የወሲብ ቅሌትና በመሳሰሉ ጎደሎ ዜናዎች ምክንያት በሀገራቸው ህዝብ ተሳትፎ የሚካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ ትክክለኛ ነባራዊ ሁኔታ መግለጽ በእጅጉ ተስኗቸው ነበር፡፡

በመሆኑም የኤሽያ የሬዲዮና ቴሌቭዥን ባለሙያዎች ስሜት ቀስቃሽና ለገበያ ውድድር ብቻ በሚያገለግሉ ዜናና ፕሮግራሞችን በመስራት ላይ ብቻ ተጠምደው ትክክለኛ የሀገራቸውን ልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ማገዝ እንዳልቻሉ በመረጃዎች አስደግፎ ያሳየናል ፡፡

መላው ኤሽያዊያን በራሱ ጥረት ከድህነት ለማምለጥ የሚተጋውንና ነገን በዛሬ ጥረቱ ለማየት የሚፍጨረጨረውን ትግል አንዳች ሊያግዘው አልቻለም ነበር ፡፡ በኤሽያ ሚዲያ የአዳዲስ ቴክኒዮሎጅ ሽግግር ፍላጎቱን ፤ በገጠርና ከተማ መካከል ያለውን ክፍተት ድልድይ ሁኖ ለማገናኘት ዝግጅት የጎደለው እንዲሆን በገበያ አክራሪዎች ዘንድ ያልተደረገ ጥረት እንዳልነበር ማስሎግ ማስረጃ አሰደግፎ ያሳየናል፡፡

"ሁሉም ነገር ለገበያ ይገዛ !" የሚል አስተሳሰብ ከኮሎናይዜሽን በኋላ በአገሬው ህዝብ ጥረት ልማትና መልካም አስተዳደር አመጣለሁ ብሎ በተነሳው የኤሽያ መሬት ዘንድ ተቀባይነት የለውም ፤ የሚለው ፕሮፌሰር ማስሎግ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራ እንደየ ሀገሩና ባህሉ ልክ መተግበር አለበት እነጅ ፤ በሌበራል ቲዎሪ መስፈሪያ የሁሉም ሀገር የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራ መስተናገድ የለበትም የሚል ቀጥተኛ አቋም አራምዷል፡፡ ተሳክቶለታልም፡፡

የልማት ኮሙኒኬሽን አስተምህሮ አራማጅ ተብሎ የሚታወቀው ዊልበር ሽራም "ማስ ሚዲያ ና ናሽናል ዴቨሎፕመንት " በሚል በ *1979* ለዩኒስኮ *19* ኛው ጉባኤ ባቀረበበው ጥናት ላይ በአለም ላይ አንድ ዓይነት ይልቁንም ምዕራባዊ ብቻ

፤ የሚባል የልማትና የኮሙኒኬሽን ሞዴል በሁሉም ሀገሮች አንደማይሰራና ሀገሮች አንደየ አካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ የሚሉትን የልማትና የሚዲያና ኮሚኒኬሽን ሞዴል መርጠው ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ ይመክራል፡፡

በ *1970* እንዲሁም በ *1980* ዎቹ ዩኒስኮ ባዘጋጃቸው ልዩ ልዩ መድረኮች ከሶስተኛው ዓለም ሀገር የተወከሉ ተሳታፊዎች የመረጡትና ይበጀናል ያሉት ብሄራዊ የኮሙኒኬሽን ፖሊሲም ይህንኑ የዊልበር ሸራምን / ሀሳብ የሚደግፍና የሰጭና ተቀባይ የኮሙኒኬሽን ሞዴል ከቁምነገር የማይቆጥር ነው፡፡

እነዚሁ ምሁራን የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራ ለልማት ዕቅዶች አፈጻጸም ሲባል በጋራ መግባባትና ጥቅም የሚተገበር የልዩ

ልዩ ፅንሰ- ሀሳቦች ጥምረት ፤የበርካታ ባለድርሻ አካላት የአመለካከትና ፍላጎት ነጸብራቅ እንጅ የሰጭና ተቀባይ ጉዳይ አይደለም ባይ ናቸው፡፡

ዊልበር ሸራም የሶስተኛው ዓለም የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ሞት “ ዕድገትና ብልጽግና ከአውሮፓና አሜሪካ ዱካ ***/foot step/*** ይመጣል ፡፡” ብለው ማመን ሲጀምሩ ነው ይላል፡፡ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራ መልዕክት ለማስተላለፍና ለማሳመን ሲባል ከአንድ ወገን እንደ ጠብታ ዉሀ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ */ tricle down /* የሚንቆረቆር ሳይሆን ተሳትፎአዊና አንዱ የሌላውን ሀሳብ የሚጋሩበትና የጋራ መግባባት የሚደርሱበት ነው፤ ባይ ናቸው አነኚሁ ምሁር ፡ ለዚህም ልማታዊ ጋዜጠኝነት ምቹ መሆኑን በማስረዳት ፡፡

ሊበራል ሚዲያ በኤሽያ ምድር ያስከተለውን ችግር የተገነዘቡት ዶ/ር ማስሎግን ጨምሮ የኤሽያ ጋዜጠኞች ፤ ዋና አዘጋጆች ፤ አርታኢዎች ጀማሪ ሪፖርተሮች በጋራ እ.ኤ.አ ከ *1988* ጀምሮ ልዩ ልዩ የሚዲያ ዎርክ ሾፖችንና ራይቲንግ ሾፖችን አካሂደዋል ፡፡ ለመፍትሄውም የኤሽያን ትክክለኛ ማህበራዊና ፖለቲካል ኢኮኖሚ የሚያንጸባርቅ፤ ህዝቡ የነገ ልማቱን በዛሬ ጥረቱ የሚያሳየውን የልማት ጆርናሊዝም እሴቶች ከሊበራል መመዘኛዎች በተለየ መንገድ የሚመዝኑበት መስፍርት ቀርፀዋል ፡፡

እነሱም ጠቀሜታ ፤ ሳይንሳዊ አተያይ፤ ሂደት ተኮር፤ በተግባር የተፈተሸ፤ህዝብ ተኮር፤ ልማት ተኮር፤ ድሆችን ያማከለ፤ውጤት ተኮር ወዘተ… */ importance, scientific approach, process oriented, pragmatic, pro-people oriented, purposive to promot development, pro-poor bias , indepth presentation/ etc…* ናቸው፡፡

የኤሽያን እሴት መሰረት ባደረጉ የልማት ጋዜጠኝነት መሰረታዊያን በፊሊፒንስ አራት ዋና ዋና ጋዜጦች ላይ ተግባራዊ ተደረገ፡፡ በነኚህ ጋዜጦች የዜና ገጽ የሚሰጠው የልማት ዜና ሽፋን እየጨመረ የወንጀል፤የጎደሎ ዜናና የወሲብ ቅሌት ዜና ሽፋን በእጅጉ እየቀነሰ ሄደ፡፡

አራት ትላልቅ ጋዜጦች የኤሽያን የዜና እሴት መሰረት አድርገው መስራት በጀመሩበት የመጀመሪያ አመት ማለትም እ.ኤ.አ በ *1999* መጨረሻ የተካሄደ ጥናት እንደሚያሳየው የአስተዳደርና ፖለቲካ *25%* ፤ስፖርት *14%*፤ የኢኮኖሚ ዘገባ *13%* ውጭ ጉዳይ ሳይንስና ቴክኒዮሎጅ *16%* ለሌሎች ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች *25* ፤ ወንጀል *7%* ሽፋን መስጠታቸውን እናያለን፡፡

ከስድስት አመት በኋላ እ.ኤ.አ በ *1995* በ *13* ትላልቅ ጋዜጦች በሚሰሩ *116* ኤዲተሮችና ሪፖርተሮች ላይ በተደረገ ተመሳሳይ ጥናት ለልማትና ኢኮኖሚ ዘገባ *18 %* ለመንግስትና አስተዳደር፤ *11 %*፤ ለሳይንስና ውጭ ጉዳይ *13* ፤ ለስፖርት *13%* ለመዝናኛ *11%* ለሌሎች ልዩልዩ ፕሮግራሞች *25 %* ሲሰጡ ፤ ወንጀል ዜና ሽፋን ወደ *9 %* ፤ መውረዱን እናያለን፡፡

ዶ/ር ማስሎግ በጥናቶቹ ከረጅም ጊዜ ሰሚናር ፤ ውይይትና ሙያዊ ትብብር በኋላ የኤሽያ መገናኛ ብዙሀን ከገበያ አክራሪው የሊበራል ሚዲያ ተጽዕኖ ተላቀው ለሀገራቸው የልማትና መልካም አስተዳደር እጅግ ጠቃሚና አጋዥ የሆነውን የልማት ጋዜጠኝነት በአንድ ቅኝት ሲያዜሙት ያሳየናል ፡፡

የልማት ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን በህንድ ፤በፊሊፒንስ፤ ሲንጋፖር ፤ ታይዋን በደቡብ ኮረያ ወዘተ… የተሳካ የኢኮኖሚ ልማት ማስመዝገቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የብሄራዊ መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡

ከኤሽያ የሚዲያ አሰራር ተሞክሮ የምንማረው ቢኖር ከህብረተሰቡ የማህበራዊ ይዞታ ወይንም ህብረተሰቡ በተጨባጭ ከሚከተለው ማህበራዊ ፤ የአኗኗር ዘይቤ የተነጠለ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ፤ ህልውናው አንዲረጋገጥለት ከፈቀደለት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የተነጠለ የሚዲያ ዘውግ የሁከትና ብጥብጥ መሳሪያ ነው፡፡

ሚዲያው የአንድ ሀገር ፖለቲካል ኢኮኖሚ አንዱና ዋነኛው አካል የመሆኑን ያህል የሚመራበት ፍልስፍናም ከዚሁ ፖለቲካል ኢኮኖሚ የሚቀዳ ነው መሆን ያለበት ፡፡ ከምዕራባዊያን የገበያ አክራሪ ሚዲያ በሚፈስበት መንገድ አብሮ መንጎድ የለበትም ፡፡

በአገራችን ያለው ችግር በኤሽያ ከነበረውና አሁን መፍትሄ ከተሰጠው የተለየ አይደለም፡፡ በድሆችና በሀብታሞች መካከል የሚታየውን የምጣኔ ሀብት ክፍተት ለማጥበብ እንሰራለን የሚሉት ምዕራባዊያን የረድኤት ኤጀንሲዎችና ገበያ አክራሪ ሚዲያ

ተቋማት ''ፅድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ '' እንዲሉ አይደለም የመረጃና የሀብት ክፍተቱን ማጥበቡ ቀርቶ በራሳችን አቅም ድህነትን ለማሸነፍ በምናደርገው ጥረት ያልተገባ ተፅእኖ ከማሳረፍ ቢታቀቡ መልካም ነበር፡፡

በአገራችን የሚዲያ ባለሙያዎች በኩልም ልንተገብረው የምንፈልገው ከአለንበት ማህበረ-ኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ የሚዲያ ፍልስፍና ላይ የጠራ የጋራ ግንዛቤ አለመያዝ ሙያው ወይም ዘርፉ በልማታችንና በዕድገታችን ላይ ሊያበረክት የሚገባውን ድርሻ እንዳይወጣ አድርጎታል ማለት ይቻላል፡፡

ምክንያቱ በጥናት የተደገፈ ባይሆንም በአገራችን ህዝብና መንግስት እየተከናወን ያለውን አንጸባራቂ የልማትና መልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታን በመንግስትም ሆነ በግል ሚዲያ ለማጀብ የተደረገው ጥረት የህዝቡንና ህግ አውጭውን ያላረካ መሆኑ ይታወቃል፡፡

አገራችን በየቀኑና በየደቂቃው ለውጥ እያስመዘገበች ነው፡፡ ዓለም በኢኮኖሚ ድቀት በምትናጥበት ጊዜ እንኳ ሀገሪቱ በታሪኳ እጅግ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን ጀምራ በስኬት እየተጓዘች ነው፡፡ ቀጣዩ ሴናርዮም የሚያሳየን ይህንኑ ነው፡፡ ይህ የሆነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ እጅግ ጠንካራ የፖለቲካል ኢኮኖሚ የተመሰረተ መሆኑ ፤ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅዶች በይድረስ ይድረስ ወይም የፖለቲካ ስልጣን ላይ ለመቆየት ሲባል ብቻ ሳይሆን በመሰረታዊነት ድህነትን አሸንፎ የበለፀገች ኢትዮጲያን በአለም መድረክ ወደ ፊት የማምጣት ራዕይ ታቅዶ እየተሰራ በመሆኑ ነው፡፡

ለልማታዊ ጋዜጠኝነት ከዚህ ወቅት የተሸለ የተመቸ ጊዜ የለም፡፡ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች የጋራ አቋም ሊይዙ ይገባል፡፡ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በሀገራችን ነፃ ሚዲያን በመገደብ የበሰለ ዲሞክራሲ ስርዓት ማካሄድ እንደማይቻል የጸና አቋም አለው፡፡

ልማታዊ ዲሞክራሲ ስርዓታችንን አስቀጥሎ የሀገሪቱን ህዳሴ ለማብሰር የስርዓቱ አንደበት የሚሆን ሚዲያ መገንባት ደግሞ ጥያቄ ውስጥ መግባት የለበትም፡፡ መስመሩን የሚፈታተኑ ውስጣዊና ውጫዊ ተፅእኖዎችን መቋቋም የሚችል መገናኛ ብዙሀን ያስፈልገናል ፡፡ ልዩነቶቻችን የሚያከብር ብዙሀን መገናኛ፡፡ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ብሄራዊ መግባባትን የሚገነባ ተቋም ወሳኝ ነው ፡፡ የግልም ሆነ የህዝብ ሚዲያዎች የኢዲቶሪያል ልዩነት ቢኖራቸውም ምንም ያህል የሚነመዝዝ ልዩነት ቢኖራቸው ለአላማ መሳካት ከጠላትህም ጋር ቢሆን መስራት ሳይንሳዊ አስተሳሰብ መሆኑን ተገንዝበው ሊሰሩ ይገባል፡፡

በአስተሳሰብም በተግባራዊ ውጤቱም ዓለም ያደነቀውን አዲሱን ፖለቲካል ኢኮኖሚ እና በኢትዮጲያ ህዳሴ ላይ እያስመዘገበ የሚገኘውን ኢኮኖሚ -ልማትና መልካም አስተዳደር ከመዘገብ ይልቅ ለህዝብ በማይመጥኑ አጀንዳዎች

መጠመዳችን "ድንቅ የሆነ ሃሳብ ይኑርህ ፤ነገር ግን ሌሎችን ለማሳመን አቅም ይንሳህ" ። የሚለው የጥንታዊ ሮማዊያን ዕርግማን ይኖርብን ይሆን ያሰኛል?

ሀሳቤን ሳጠቃልል ወደ ተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ተመልሼ ነው። የልማት ጋዜጠኝነት በአገራችን ጊዜው ያልደረሰ ሀሳብ ፤ ወይስ የተሳካ ግብ ? ጊዜው ያልደረሰ ሀሳብም የተሳካ ግብም አይደለም ። የልማት ጋዜጠኝነት በሀገራችን ጊዜው የደረሰ ሀሳብ ነው ። ጊዜውም አሁን ነው ። ነገር ግን ያልተሳካ ግብ ነው ። ላለመሳካቱ ሁነኛ ምክንያት ላይ የውይይት ሀሳብ ቢሆን።